ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ

CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን ስነ-ምግባር ግንባታ፥ ሙስና መከላከል እና አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል የተቋቋመ የጋራ ፎረም

ጥቅምት 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# መግቢያ

የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን በተሻሻለዉ አዋጂ ቁጥር 1333/2016 የሀገራችንን ግዥ የመቆጣጣሪና ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለዉን ጥቅም እንዲያስገኝ ለማድረግ ፣በግዥ ሂደት የሚፈፀመዉን ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በርካታ ተግባርና ኃላፊነቶች የተሰጡት ተቋም ነዉ፡፡ግዥ በሀገራችን ከፍተኛ ሀብት የሚፈስበት መሆኑ ብቻ ሳይሆን ሙስናና ብልሹ አሰራር በስፋትየሚፈጠርባቸዉ ዘርፎች ተብለዉ ከተለዩ ዋና ዘርፍ ነዉ፡፡ይህን ዘርፍ ለመቆጣጠር ባለፉት ዓመታት እንደ ተቋም ሰፊ ርብርብ ከመደረጉም በላይ ግዥ በዘመናዊ ተክኖሎጂ ታግዞ እንዲከናወን ፣ በግንዛቤ ክፍተት የሚፈጠሩ የአሰራር ብልሽቶች እንዲስተካከሉና በዘርፉ ያሉ ባለሙያዎች በቂ እዉቀት እንዲኖራቸዉ የማሰልጠን የማብቃት ተግባራት በስፋት ተከናዉኗል፡፡ባሳለፍነዉ በጀት ዓመት በቀድሞ የሀገርቱ ግዥ አዋጂ ላይለስራ ምቹ ያልሆኑድንጋጌዎችን ለማሻሻልና ቀልጣፋ ዉጤታማና ከብልሹ አሰራር በፀዳ መልኩ እንዲፈፀም በርካታ ማስተካከያዎች ተደርገዉ ዉስን የሆነዉ ሀብት ለታለመለት ዓላማ እንዲዉል የበኩሉን ደርሻ ተወጥቷል፡፡

ሙስና በባህሪዉ ዉስብስብና የሁሉንም አካላት ርብርብ የሚፈልግ እንደመሆኑ መጠን በመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን የሚገኙ የስራ ክፍሎች ማለትም የስነ ምግባር መከታተያ ፣የህግ አገልግሎት ፣ የዉስጥ ኦዲት ስራ አስፈፃሚ እና ተቋማዊ ለዉጥ ስራ አስፈፃሚ በጋራ ፎረም በመመስረት የተቋሙን አጠቃላይ በአገልግሎት አሰጣጥ በመልካም አስተዳደር እና ሙስና ጉዳዮች ላይ ዕቅድ በማዉጣት ለመስራት ተቋሙ የሚጠበቅበትን ሀገራዊ ተልዕኮ የሚሸከም እንዲሆንና የዉስጥ አሰራራችን የተጠናከረ ለህዝቡ በግልፀኝነትና በታማኝት አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ሁኔታ ለመፍጠር፤ ቅንጂታዊ አሰራርን ለማጠናከር፣በስነ ምግባር ግደፈት የፈጠሩ ሰራተኞችን ለማረምና ለማስተካከል ይህ የጋራ ፎረም አደረጃጀት ተመስርቷል፡፡

# የጋራ ፎረሙ አደረጃጀት ዓላማ

- በመንግስት ቻዥና ንብረት ባለስልጣን ዉስጥ ሙስናና ብልሹ አሰራር እንዳይፈጠር ፣ አሰራር እንዲጠበቅ የሙስናሥጋትተጋላጭነትንመገመገምእና የመፍትሔ ሀሳብ ማመንጨት ፣ የተፈጠሩ ችግሮች ላይ እርምጃ እንዲወስድ በማድረግ ሙስናና ብልሹ አሰራርን የሚፀየፍ አመራርና ሰራተኛ እንዲፈጠር ማድረግ ነዉ፡፡

# የፎረሙአስፈላጊነት

- የሀገራችን ብልፅግና ጉዞን ወደኂ ላየ ሚጎትተዉን ሙስናና ብልሹ አሰራር በአንድ የስራ ክፍል እና በተወሰኑ ግለሰቦችና ሰራተኞች ማሳካት የሚቻል አለመሆኑና በተቋሙ የሚገኙ የስራ ክፍሎች በጋራ ተቀናጂተዉና ተናበዉ በእቅድ እንዲመሩት ለማድረግ በፎረም መደራጀት አስፈላጊ ስለሆነ ነዉ።
- በተቋሙ ሊከሰት ይችላላ ተብሎ የሚታሰበውን የስነ ምግባር ብልሽት በመቅረፍ ለተገልጋዮች ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጥ፥ በተቋማችን ሙስናን የመከላከሉን ተግባር በእቅድ እንዲመራና የሚመለከታቸው አካላትም የበኩላቸውን ድርሻ እንዲውጡ ለማድረግ የሚያስችል ነው።
- በአጠቃላይ ሌብነትና ሳይሰሩ የመበልፀግ አባዜ፥አገልግሎትን በገንዘብ ለመሸጥ የመሞከር ሁኔታ በተቋማችን እንዳይከሰትና የተፈጠሩ ችግሮችንም በጋራ ለማረም እድል ስለሚሰጥ በፎረም ተደራጂቶ የተቋሙን ጠቅላላ ሰራተኛ በማስተባበር ተቋማችን የሚያከናዉነዉን የተቆጣጣሪነት ሚናን ከፍ የሚያደርግ ስለሆነ በጋራ ፎረም መደራጀት አስፈላጊ ነዉ።

## በፎረሙ የሚካተቱ የስራ ክፍሎች ተግባርና ኃላፊነት

የፎረሙ አባላት የሚከተሉ ሲሆኑ፡-

1. የስነ ምግባር መከታተያ ስራ አስፈፃሚ---------------------የፎረሙ ሰብሳቢ
2. የህግ አገልግሎት ስራ አስፈፃሚ ----------------------------የፎረሙ ፀሐፊ
3. የተቋማዊ ለዉጥ ስራ አስፈፃሚ-------------------------------የፎረሙ አባል
4. የኢዱት ስራ አስፈፃሚ---------------------------------------------የፎረሙ አባል

## የስነ ምግበር መከታተያ ስራ ክፍል ተግባርና ሀላፊነት

- ፎረሙን በሰብሳቢነት ይመራል
- የፎረሙን ዓመታዊ ዕቅድ ያዘጋጃል
- በተቋሙ ዉስጥ ልከሰቱ የሚችሉ ብልሹ አሰራርና ሙስና ቀድሞ መረጃ በመሰብሰብ በፎረሙ አባላት እያስገመገመ ቅድመ መከላከል ስራ ይሰራል
- የስብሰባ ቀናትን በአባላቱ ያስወስናል

- የጥቆማ መረጃዎችን ይቀበላል ያደራጃል ለፎረሙ አባላት ያቀርባል
- የተለያዩ የስነ ምግባር ግንባታ ሙስና መከላከል ስልጠናዎችን ያመቻቻል ያሰለጥናል
- ከፎረሙ ጋር የሙስና ስጋት ተጋላጭነት ጥናት ያካሂዳል
- የተገኙ መረጃዎችን መነሻ በማድረግ የተቋሙን ኃላፊ ያማክራል የመፍትሔ ሀሳብና ዉሳኔ እንዲሰጥበት ያደርጋል
- ወቅታዊ ሪፖርት ለተቋሙ በላይ ኃላፊ ለፀሬ ሙስና ኮሚሽን እንዲሁም ለፎረሙ ያቀርባል

## የህግ አገልግሎት ስራ አስፈፃሚ ተግባርና ኃላፊነት

- ፎረሙን በፀሐፊነት ይመራል
- ቃሌ ጉባኤ ይይዛል
- በተቋሙ የተፈጠረ ሙስናና ብልሹ አሰራር በህግ አግባብ ይመረምራል፤ ሂደቱን በመከታተል እና ተጣሪቶ እርምጃ እንዲወሰድ ያደረጋል
- በፎረሙ ዉስጥ የታቀዱ ተግባራትን በአግባቡ መፈፀማቸዉን ይከታተላል
- የጨሬታና ለሎች ህደቶች በህጋዊነት መፈፀም አለመፈፀማቸዉን ይከታተላል
- በፍርድ ቤት የተያዙ የተቋሙ ጉዳዮችን በባለበትነት ይከታተላል፥
- በቅጥር በደረጃ ዕድገት በተለያዩ መንገዶች በሰራተኞች ላይ አድሎአዊ አሰራር እንዳይኖር ክትትል ያደርጋል የተጣራ መረጃ ስኖር ከሚመለከታቸዉ ጋር በመሆን ሂደቱ እንዲቆም ያደርጋል
- ሰራተኞች በብሔር በሀይማኖት፥በጓደኝት እንዳይጠቃቀሙ አሰራሮችን ይፈትሻል ይመረምራል የተፈፀሙ ጉዳዮች በተጨባጭ ካሉ እርምጃ እንዲወሰድ ለፎረሙ አባላት ያቀርባል
- የሙስና ተጋላጭነት ጥናት ዉጤት መሰረት ለፎረሙ አባላት ከህግ አንፃር የመፍትሔ ሀሳቦችን ያቀርባል

## የተቋማዊ ለዉጥ ስራ አስፈፃሚ ተግባርና ኃላፊነት

- የሪፎርም አቅጣጫዎች በአግባቡ እና በትክክል በተቀመጠዉ አሰራር እየተፈፀመ መሆኑን ይከታተላል ይገመግማል

- በተቋሙ የሚዘና ስረዓት ላይ የሚታዩ ብልሽቶች በመለየት በመለየት እንዲስተካከሉ ይሰራል
- የማበረታቻ የእዉቅና አሰጣጥ ስረዓት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ስለመፈፀሙ ይገመግማል
- የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን ለማሻሻል የተቀመጡ ስታንዳርዶች እንደት እየተፈፀሙ እንደሆነ ይገመግማል ሪፖርትም ያደርጋል
- የአስተያየት መስጫ ሳጥኖች ዉስጥ ያሉ ቅሬታዎችና አስተያየቶችን በፎረሙ አባላት ያስገመግማል እንዲታረሙና እንዲስተካከሉ የተባሉ ጉዳዮችን ለስራ ክፍሉ በግብረ መልስ ይሰጣል
- የተቋማችንን አሰራር በግልፅ የሚያሳዩ መረጃዎች በቦርድ በስክሪኒና በተለያዩ መረጃ መስጫዎች ላይ ያሳያል
- የስራ ክፍሎችን ለተገልጋዩ ምቹ የማድረግ ዕቅድን ይተገብራል

## የኦዲት ስራ አስፈፃሚ ተግባርና ኃላፊነት

- በበጀትና ንብረት አጠቃቀም ላይ ሊከሰት የሚችለውን ብልሹ አሰራርና ተግባራትን ለመከላከል ጥብቅ የውስጥ ኦዲት ስራያ ከናዉናል
- የሰራተኞችን የስነ ምግባር ደረጃ ማሳደግና የተጠያቂነት ስርአት እንዲሰፍን ይሰራል
- በኦዲት ምርመራ ወቅት በሙያዊ ስነ-ምግባር መሰረት የኦዲትም ሚስጥር እንዲጠበቅ ያደርጋል
- የውስጥ ኦዲት ግኝቶች ላይ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ እና አፈጻፀሙን ለፎረሙ እና ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያቀርባል
- ከአሰራር ውጭ የተሰሩትን ስራዎች በህግና በአሰራር ማንዋሉ መሰረት ሂደቱን ኦዲት ያደርጋል
- የውስጥ ኦዲት በማጠናከር የክትትልና ተጠያቂነት ስርአት እንዲሰፍን ያደርጋል፣
- በተቋማችን ከንብረት አጠቃቀም ከቅጥርና ደረጃ ዕድገት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ኦዲት በማድረግ ሪፖርት ያቀርባል

## የፎረሙ አሰራር

- በየወሩ እየተገናኜ የጋራ ዕቅዶችንና ለሎች አስቸኳይ ጉዳዮችን ይገመግማል።
- ለተቋሙ ኃላፊ የፁሑፍና የአካል ሪፖርት ይቀርባል።
- የሚጣሩ ጉዳዮችን በፎረሙ አባላት የማጣራት ስራ ይሰራል።
- ለስራ ክፍሎች እንደአስፈላጊነቱ በአገልግሎት አሰጣጥ እና ለሎች ጉዳዮች ላይ ግብረ መልስ ይሰጣል።

# ማጠቃለያ

በመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን የመልካም አስተዳደርና ሙስና መከላከል የጋራ ፎረም ከላይ በተገለፁ ዋና ዋና ጉዳዮች በጋራ ዕቅድ አዉጥቶ ለመስራት በተለይ ሀገራዊ እና ተቋማዊ የተቀናጀ የፀሬ ሙስና ስትራተጂ ወደ መሬት ለማዉረድ ከወትሮ በተለየ ቅንጂትና አንዲነት ለመስራትና ለተቋሙ የበላይ አመራር ወይም በተቋም ደረጃ ለተቋቋመዉ የፀሬ ሙስና ካዉንስል በየጊዜዉ ምክሬ ሀሳብና ሪፖርት እንዲሁም በተቋሙ ሁሉም የስራ ክፍሎች ላይ የተጠናከረ ክትትል ድጋፍ ለማድረግ ይህንን ፎረም ተመስርቷል።

ጥቅምት 2017 ዓ.ም

የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን